# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ.ም.**

**በመለስ ዛቻ እና ማስፈራሪያ ህዝቡ በእጅጉ አዘነ፤**

**ወያኔ አዳዲስ አባሎችን ለመመልመል በሚሊዮን የሚቆጠር**

**የሀገሪቱን ገንዘብ መመደቡ ተጋለጠ፤**

**ሲኖዶሱ በንትርክ እና በጭቅጭቅ ሲወዛገብ ሰነበተ፤**

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የቡድኑን አቋዋም በገለጸበት እለት የሰነዘረውን ማስፈራሪያ ፍጹም አምባገነንነት የነገሰበት ንግግር ነበር በማለተ ተተቸ።

በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉትን የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች የውስጥ ችግርን ለማርገብና አቅጣጫ ለማስቀየር ሲባል ብቻ የአሸባሪነት ታፔላ እየለጠፉ ለእስር መዳረግ በሁዋላ ችግሩን ማባባስ እንጂ አያረግበውም፤ በአፍሪካ እየተደረገ ያለውን የአምባገነኖች ውርደት ከነ ሆስኒ ሙባረክና ሙአመር ጋዳፊ መማር ብልህነት ነው በማለት አንዳንድ የመድረክ አመራር አባላት ተናግረዋል።

አንዳንድ የመድረክ አመራሮች በአሸባሪነት ከተፈረጁት ድርጅቶች ጋር በመሆን የመንግስትን ተቋዋም ለማፍረስ ይሞክራሉ ለዚህም በቂ ማስረጃ አለን እያለ ሲደነፋ የነበረው መለስ ዜናዊ መልሶ የተጠናከረ መረጃ እስክናገኝ ድረስ ነው የምንጠብቃቸው እያለ ሲዘላብድ መዋሉም ለከፍተኛ ውርደት መዳረጉን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ከህዝቡ ያገኘውን ጥቆማ ገልፆዋል።

በማን አለብኝነት አፉ ያመጣለትን ብቻ ሲለፍፍ የዋለው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ህዝብ ምን ይለኛል ሳይል አሳፋሪ የሆነ ፍጹም ኢትዮጵያዊ ጨዋነት የጎደለው አጉራ ዘለል ባሕሪ የተጠናወተው ንግግር ማድረጉ በእጅጉ የሚያሳዝን በማለት በርከታ ዜጎች አስተያየት የሰጡ ሲሆን ያበተለይ እራሱ ፈንጂ እያፈነዳ ንጹሀን ዜጎችን እየገደለ መልሶ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ላይ ጣቱን መቀሰሩ ግዜው ያለፈበት ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ማግኛ ነው ሲሉም በንዴት ሲገልጹ አንደተደመጡ ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ለመገንዘብ ችሏል።

በሀገሪቱ በ60 ዓመታት ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ርሀብ ተከስቶ ዜጎች እንደቅጠል እየረገፉ በይፋ እየታየ እና እየተገለፀ ባለበት በዚህ ግዜ አይኔን ግንባር ያድርገው በማለት ሽምጥጥ አድርጎ እየካደ ከመሆኑም በላይ በከተማው የኑሮ ውድነት እጅግ ከመጠን በላይ እያሻቀበ መሆኑን እያወቀ ግዜ ለማግኛ እና የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሲል ብቻ ዜጎችን በአሸባሪነት እየፈረጀ ለእስር መዳረጉ ችግሩን ያባብሰዋል እንጂ አይቀርፈውም ሲሉም ነዋሪዎች መግለጻቸውን ዘጋቢያችን ገልፆዋል።

ዛሬም ፍርሀቱ አልለቅ ያለው ወያኔ ዜጎችን ከየመንደሩ እየለቀመ ለእስር እየዳረገ መሆኑን ከተለያዩ ከተሞች የሚደርሱን ጥቆማዎች ያስረዳሉ። መለስ ዜናዊ መግለጫ በሰጠ በጥቂት ቀናት ውስጥ የቀድሞ የህወሀት ታጋይ የነበረው አሁን የመድረክ አባል የሆነው አማረ ተወልደ የተባለው ግለሰብ በወያኔ የጸጥታ ኃይሎች ታፍኖ መታሰሩ ታውቆዋል።

የመድረክ አባሉ የትግራይ ተጠሪው አማረ ተወልደ በሁመራ ከተማ ቅሰቀሳ ስታደርግ ተይዘሀል በሚል በዚያው ሁመራ ለእስር የተዳረገ ሲሆን ሌሎችም ግንኙነት አላችሁ ተብለው እንደታሰሩም ከሁመራ የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል።

በሌላ ዜና የወያኔ ቡድን በውስጡ በተፈጠረ ትርምስ ምክንያት ግራ ተጋብቶ እዚያና እዚህ እየረገጠ ባለበት በዚህ ግዜ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ነባር እና አዳዲስ አባሎቹ እየከዱት መምጣታቸውን ተከትሎ ሌሎች አባሎችን ለመመልመል ከፍተኛ በጀት መመደቡ ታወቀ።

በጥቅምና በተለያዩ ዘዴዎች ጠልፎ ያስገባቸው አባሎቹ የወያኔን ገመና ውስጡ ድረስ ዘልቀው በማወቃቸው...... አብረው ሊቀጥሉ እንደማይችሉ በመረዳታቸው..... በገዛ ፈቃዳቸው በይፋ እየለቀቁ በመምጣታቸው....... ድንጋጤና ፍርሀት ያደረበት የወያኔ የአመራር ቡድን ሰሞኑን አዲስ ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ ሊጀምር መሆኑ ታውቆዋል።

በአዲስ አበባ የተጀመረው ይሄው አዲስ ስልታዊ የአባላት ቁጥር ማብዛት የሚለው እንቅስቃሴ ሰሞኑን በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገሪቱ ገንዘብ ወጪ በማድረግ የሴቶች ሊግ፤የወጣቶች ሊግ ፤ የአማራ ልማት ማህበር...... የትግራይ ተወላጆች በሚሉና በሌሎችም ዘዴዎች ዜጎችን እያስገደደ አባል ለማድረግ መዘጋጀቱ ታውቆዋል::

በወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ውስጥ ሳይቀር የበላይ እና የበታች የነገሰበት አሰራር እንዲሁም ፍጹም አድልዋዊ ስርዓት በስፋት የሰፈነበት መሆኑን በመገንዘባቸው ከየዩኒቨርስቲው ውስጥ ተመልመለው ስራ ተሰጥቶዋቸው የነበሩ ወጣቶች በሙሉ ከአባልነታቸው በተጨማሪ የተመደቡበትን ስራ እየለቀቁ እራሳቸውን በማግለላቸው ከፍተኛ ፍርሀት የነገሰበት ይሄው ቡድን ሰሞኑን በተለያዩ አዳራሾች ዘመቻ መጀመሩ ታውቆዋል::

አብዮታዊ ዲሞክራሲ የተሰኘው መመሪያ ላይ ላዩን ህዝቡ እንዲያውቀው የሚደረገው በጥሩ ቃል ተከሽኖ የሚቀርብ ሲሆን በውስጥ ለእኛ የሚሰጠንና እንድንተገብረው የሚደረገው ደግሞ ሀገርን እና ህዝብን የሚጎዳ ብቻ ሳይሆን ከጥቅም ውጭ የሚያደርግ ሆኖ በማግኘታችን ይሄንን የመሰለ ውንብድና አብሮ መፈጸሙ ተገቢ ባለመሆኑ ስራችንን እና አባልነታችንን በገዛ ፍቃዳችን ለቅቀናል በማለት የመልቀቂያ ደብዳቤ እያስገቡ በመሆናቸው ወያኔ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ድንጋጤ ላይ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል::

ከዚህ ቀደም ከ18 ዓመት በላይ በወረዳና በዞን የካቢኔ አባልነት ጭምር ሲያገለግሉ የነበሩ የወያኔ ቀንደኛ ካድሬዎች አድልኦው ከነገ ዛሬ ይሻሻላል ብለን በትዕግስት በንጠብቅም እየባሰ በመምጣቱ አብረን አንዘልቅም በማለት ስልጣኑንም ስራውንም ትተነዋል ያሉት እነዚሁ የወያኔ አባል የነበሩ ግለሰቦች ዛሬ ደግሞ ከዩነቨርስቲ ውስጥ በግዳጅ እየመለመለ የሰገሰጋቸው ወጣቶችም የወያኔን ገመና በማወቃቸው እርቃኑን እያስቀሩ በይፋ እየለቀቁ መገኘታቸው ዛሬም ደደቢት በረሀ የሚሰራው ሸፍጥ እንዳለ መሆኑን በብስጭት እየተናገሩ ናቸው::

በቅርቡ እነ መለስ ዜናዊ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ ካድሬዎች ላይ ጥብቅ ግምገማ ይደረግ ብለው በወሰኑት መሰረት ቀን ከሌሊት...... ላይ ታች ቢሉም ከጥቂቶቹ በስተቀር በሙሉ በወያኔ መሰሪ አካሄድ ያልተደሰቱ በመሆኑ ግምገማው ላይ ሳይገኙ ከመቅረታቸውም በተጨማሪ በግምገማው ላይ የተገኙትም ከፍተኛ ተቃውሞ እያሰሙ በመገኘታቸው ግምገማው ላልተወሰነ ግዜ እንዲቋረጥ መደረጉን እነዚሁ አባሎቹ ገልጸዋል::

ዛሬ የወያኔ ቡድን ግራ ሲገባው የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ በሴቶች ሊግ በኩል በየቀበሌውና በየዞኑ ብሎም በየመንደሩ እየዞሩ ሊያሳምኑ እና አባሎችን ሊያፈሩ ይችላሉ የተባሉ የቤት እመቤቶች ጭምር በቀን 200 ብር የውሎ አበል እየተከፈላቸው ስራ እንዲጀምሩ ቢደረግም ከውስጥ ደግሞ ነባር የከተማ አባሎች እየለቀቁ መሆኑ ታውቆዋል::

የወጣቶች ሊግ የተባለው የወያኔ ክንፍ በበኩሉ ከዚህ ቀደም ቀንደኛ የወያኔን ዓላማ አስፈጻሚ የነበሩትን እነ ታጠቅ የተባሉትን የደለበ ገንዘብ እየሰጠ የግል ድርጅት ባለቤት እያደረገ ከሸኘ በሁዋላ አሁን ያሉትን ወጣቶች ዓላማውን እንዲያስፈጽሙለት ቢሞክርም ከስራ ይልቅ ጥቅም ፈላጊ

በመሆናቸው ያሰበው ሳይሳካ በመቅረቱ አዲስ ስልት ሊከተል መገደዱን እነዚሁ የወጣት ሊግ አባሎች ገልፀዋል::

ህዝቡ በከፍተኛ የኑሮ ቀውስ ውስጥ እየዳከረ እንደሚገኝ የሚያውቁት እነ መለስ ዜናዊ የህዝቡን ችግር በጥቂቱም ቢሆን ሊቀርፍለት የሚችለውን ገንዘብ ከሀገሪቱ ካዝና እየወሰዱ ለአባል ምልመላ በሚል መበተናቸው አሳዛኝ እና አሳፋሪ ከመሆኑም በተጨማሪ ለህዝቡ ካላቸው ንቀት የተነሳ የሚያደርጉት መሆኑንም እነኚሁ የወያኔ አባል ወጣቶች በንዴት ይገልጻሉ::

የአማራ ልማት ማህበር በበኩሉ አባሎቹን በግዴታ መዋጮ እንዲያዋጡ ሲያስገድድ የነበረ ቢሆንም ሁሉም አቁዋም በመያዛቸውና የወርሀዊም ክፍያ በማቁዋረጣቸው በአዲስ ስልት እንደገና ለመመልመል በዝግጅት ላይ ሲሆን ለዚህ ስራ የሚውል ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ መመደቡ ታውቆዋል::

አዲሱ የምልመላ ስልት እንደሆነ የተነገረለት ዘዴ መታወቂያ እየሰጠ ችግር ቢያጋጥምህ በዚህ ስልክ ደውለህ ሊቀረፍልህ ይችላል እያሉ ከሌሎች ዜጎች የተለዩ እንደሆኑ በማስመሰል የአባል ቁጥሮቹን ለማብዛት የተዘጋጁ መሆኑም ታውቆዋል::

ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ ሁኔታ በጥቅማጥቅም ተይዘው ተመልምለው የነበሩና ስራ ተሰጥቶዋቸው የነበሩት የአማራ ልማት ማህበር አባሎች በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ሴራ ፍጹም አንገሽግሾዋቸው ለቅቀው የወጡ መሆኑን የገለፀው የአባሎቹ ጥቆማ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ ፍፁም አምባገነንነት የሰፈነበት በመሆኑ ከወያኔ ጋር አብሮ መጉዋዙ ከመቼውም ግዜ በላይ አስቸጋሪ ነው ሲሉም ጨምረው አስረድተዋል::

በመጪው ዓመት ለሚደረገው የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ምርጫ ከወዲሁ በጎጥ እና በቡድን በየሰፈሩ እየዞሩ ህዝቡን እንዲያደራጁ ተብለው በዩኒቨርስቲ የሚማሩ አባሎች እና አመራሮች ትምህርታቸውን እንዲያቁዋርጡ መመሪያና ትዕዛዝ የተላለፈላቸው ቢሆንም እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ አንዳቸውም ተግባራዊ ካለማድረጋቸውም በተጨማሪ የወያኔ የበላይ ክፍል ራስ ወዳድ በመሆኑ ከእነሱ ጋር አንቀጥልም እያሉ መልቀቂያ እያስገቡ በመሆኑ ለወያኔ መሪዎች ትልቅ የራስ ምታት እንደፈጠረባቸውም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

ነባር አባሎች ሲለቁባቸው አዳዲስ አባሎችን ለመመልመል ደፋ ቀና እያሉ የሚገኙት የወያኔ ቁንጮ ባለስልጣናት የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባን ጨምሮ ሌሎች ሶስት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ከሸኙ በሁዋላ አሁንም ሌላ ከፍተኛ የከተማዋን ሹም ማባረራቸው ታውቆዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ ሹማምንት ላይ የተጀመረው ምንጠራ ሰሞኑን ቀጥሎ የከተማዋ አፈ ጉባዔ የነበረው ይርጉ አዲሱ የተባለው ካድሬ ከስልጣኑ ሲነሳ ሌላ ያልጠገበው ታቦር ገ/መድህን የተባለ ነባር የበረሀ ታጋይ መሾሙ ታውቆዋል::

በወያኔ ውስጥ የተጀመረው ሹም ሽር እና እገዳ በስፋት ቀጥሎ በአንድ ቀን ውስጥ ብዙ ባለስልጣናት ከስልጣናቸው ሲነሱ በምትካቸው ለግዜው ይቀመጡ እየተባለ ብዙ ልምድ

የሌላቸውና ህዝቡ ጨርሶ የማያውቃቸው ካድሬዎች እየተመደቡ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይ በቀበሌና ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎች በትርምሱ ሳቢያ አገልግሎት መስጠት ማቆማቸው ታውቆዋል፡፡

ጭንቅና ምጥ ውስጥ የገባው የመለስ ዜናዊ አስተዳደር ከላይ ከቁንጮ ባለስልጣናት ጀምሮ እስከ ዝቅተኛው ክፍል ድረስ በጥርጣሬና በጥላቻ ካድሬዎቹን እያነሳና እያባረረ እንዲያም ሲል ዘብጥያ እየከተተ የሚገኝ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ እየተደረገ ያለው ሹም ሽረት አሁንም እንዳላበቃ እየተነገረ ይገኛል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ከፍተኛ አመራሮችን ጠርጎ እየጣለ የሚገኘው የወያኔ ቡድን ከስልጣኑ ከተነሳ አራት አመታትን ያስቆጠረውን የቤንሻንጉል ክልል ፕሬዝዳንት ያረጋል አይሸሹምን ጨምሮ ብዙ ባለስልጣናትን በሙስና ሰበብ ቃሊቲ እስር ቤት እያጎራቸው መሆኑ በወያኔ ውስጥ አንጃ መፈጠሩን አመላካች ነው የሚሉ ወገኖች በርካታ ናቸው፡፡

ከአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባነት የተነሳው ከፍያለው አዘዘም ከአንድ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር ጋር በምስጢር ሲደራደር እና የራሱን ሴል በወያኔ ውስጥ ዘርግቶ ተገኝቶዋል ተብሎ በደህንነቶች ለመለስ ሪፖርት በመደረጉ በስራ ብቃት ሽፋን ከስልጣኑ እንዲነሳና የቁም እስር እንዲሆን በተወሰነው መሰረት ዛሬ በቤቱ ውስጥ ተገድቦ እንዲቀመጥ ልዩ ትዕዛዝ እንደተላለፈበትም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የጦር ጄኔራሎቹን ከታጣቂ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ጋር ግንኙነት አላችሁ ተብለው በታሰሩበት ወቅት በሰራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ ችግር አጋጥሞዋቸው የነበሩት እነ መለስ ዜናዊ አሁንም ይህን ግለሰብ ከፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ጋር ግንኙነት ሲያደርግ ተያዘ ተብሎ በይፋ ቢነገር ሁሉም ያኮረፈ የወያኔ አባል አቁዋሙን ሊቀይር ይችላል ተብሎ ስጋት ስላሳደረ በስራ ብቃት ማነስ ሽፋን እንዲነሳና በቤቱ ውስጥ ተወስኖ እንዲቀመጥ መደረጉን የደረሰን ጥቆማ ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡

በዚህም የተነሳ በወያኔ ቡድን ውስጥ ያልታወቀበት ከፍተኛ የተቀጣጠለ እሳት እንዳለ የሚያሳይ ነው ሲሉም የተቃዋሚ አመራሮችም ሆኑ ምሁራኖች ግምታቸውን እየሰነዘሩ ይገኛሉ፡፡

በመጨረሻም በአባ ጳውሎስ የሚመራው ሲኖዶስ ከመቼውም ግዜ በላይ ከፍተኛ ትርምስ እና ንትርክ ውስጥ በመግባቱ ከጥቅምት 13 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ  እስከ ዓርብ ጥቅምት 17 ቀን 2004 ዓ.ም  ድረስ የተደረገው ስበሰባ ያለስምምነት ሊቆይ እንደቻለ ተጠቆመ፡፡

ከቤተክህነት ምንጮች ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ እንደገለፀው ከሆነ ሰሞኑን በተጀመረው ዓመታዊ ሲኖዶስ ስብሰባ ላይ እጅግ አከራካሪ ጉዳዮች ከመነሳታቸውም በተጨማሪ በአባ ጳውሎስ ላይ ከፍተኛ ነቀፌታ ሲሰነዘርባቸው እንደሰነበተም ምንጮቹ ጠቁመዋል፡፡

በዘር ሀረግ ብቻ ያውም የአድዋ ተወላጅ ተመርጦ ሙሉ ለሙሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ቤተክህነትን ለመቆጣጠር ሌት ከቀን እየሰሩ ያሉት አባ ጳውሎስ በአሁኑ ሰዓት

በፈፀሙት አድሎአዊ አሰራር ላይ ከፍተኛ ነቀፌታና ትችት ከጳጳሳቱ እየደረሰባቸው መሆኑም ታውቆዋል።

ሰኞ ዕለት የተጀመረው የሲኖዶሱ ጠቅላላ ጉባዔ እጅግ በርካታ ጉዳዮች ላይ ይመክራል ......ለእምነቱ ጠቃሚ የሆኑ ውሳኔዎችን ያሳልፋል.....በዘር ሀረግ ላይ የተመሰረተውን የአባ ጳውሎስ ሰንሰለት ይበጥሳል ......በአስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነታቸው ላይ ውሳኔ ይሰጣል ተብሎ በጉጉት ቢጠበቅም ሲኖዶሱ በአባ ጳውሎስ ቀረጣ ስልት የታሰበውን ያህል ውሳኔ ሳያሳልፍ መቅረቱ ታውቆዋል።

አባ ጳውሎስ ቤተክህነትን እያመሱ ከመሆኑም በላይ ጳጳሳቱን በአሉባልታ እርስ በርስ እያጋጩ አንዱን ደጋፊ ሌላውን ተቃዋሚ እያደረጉ በመሆናቸው እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ጳጳሳት ድርጊቱን ከማውገዛቸውም በተጨማሪ በግልጽ ሲነቅፉዋቸውና ሲቃወሙዋቸው እንደሰነበቱ ከምንጮቹ ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

በተለይ ከአቡነ ሳሙኤል ጋር የተጀመረው ፍጥጫ ዛሬም እንደ አዲስ ተፋፍሞ የቀጠለ ሲሆን የአባትነት ክብር በመሀከላቸው ጠፍቶ አንተ አንተ እየተባባሉ ሲወነጃጀሉ ያደመጡ ጳጳሳት እጅግ ከማዘናቸው የተነሳ ስብሰባ አቁዋርጠው እስከ መውጣት መድረሳቸውን የቤተክህነት ምንጮች ጥቆማ አስረድቶዋል።

በቅርቡ በአሜሪካን ሀገር ተመድበው ሲሰሩ የነበሩ ሁለት ጳጳሳት የአባ ጳውሎስን ሲኖዶስ ከመተቸታቸውም በተጨማሪ በዘር ሀረግ ላይ ተመስርቶ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ አስቸኩዋይ ውሳኔ ሊያሳልፍ ይገባል ሲሉ ለሲኖዶሱ አቤቱታ ማቅረባቸው ታውቆዋል።

አቡነ አብርሀም (የዲሲው) እና አቡነ ኤምስጣጢዎስ የካሊፎርኒያው(ሎስ አንጀለስ) ከአባ ጳውሎስ ጋር በፍጹም መስራት የማይቻልበት ደረጃ የደረስን በመሆኑ ከሲኖዶሱ ጋር ለመቀጠልም ሆነ ላለመቀጠል እንድንችል ጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ እንዲሰጠን ሲሉም ለሲኖዶሱ ቅሬታቸውን ማቅረባቸው ታውቆዋል።

ከስድስት ወራት በላይ ደሞዝ ሳይከፈላቸው ሲሰሩ እንደቆዩ የገለፁት እነዚሁ ሁለት ጳጳሳት ይሄን ሁሉ ተቁዋቁመን እየሰራን እያለ እኛ ሳናውቀውና ሳንሰማው በአሜሪካን ሀገር ያለነውን ጳጳሶች ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው አባ ጳውሎስ የአድዋ ተወላጆች የሆኑ ሶስት ሰዎችን ልከው ስውር የደህንነት መዋቅር ዘርግተው መገኘታቸውን ደርሰንበታል ሲሉም አጋልጠዋል።

በሁለቱ ሲኖዶስ መሀከል የተጀመረው እርቅ እንዳይቀጥል አባ ጳውሎስ የራሴ ናቸው ያሉዋቸውንና የአድዋ ተወላጅ የሆኑትን 35 ተሹዋሚዎች የጵጵስና ማዕረግ እንዲሰጣቸው ለሲኖዶሱ ያቀረቡ ቢሆንም እስከ ዐርብ ዕለት ድረስ ጳጳሳቱ እርቁ ተግባራዊ ከሆነ ይህ ሁሉ ጳጳስ የት ሊሰራ ነው ስለዚህ ያለነው በቂ በመሆኑ አናጸድቅም በማለት ሲሞግቱ የሰነበቱ መሆኑንም ምንጮቹ አብራርተዋል።

ከዚህም ሌላ ሁለቱ ጳጳሳት አቤቱታቸውን ሀገር ቤት ላሉ ጳጳሳት በሙሉ በእጃቸው እንዲደርሳቸው በማድረጋቸው የደረሰባቸው በደልና ግፍ አሳዛኝ መሆኑን የተገነዘቡት አባቶች በአባ ጳውሎስ ላይ ቅሬታቸውን ከመሰንዘራቸው በተጨማሪ ያሉንን አባቶች በአግባቡ ሳንይዝ ተጨማሪ

ጳጳሶችን መሾሙ ተገቢ አይደለም በማለት የአባ ጳውሎስን ጥያቄ ውድቅ ማድረጋቸውም ከቤክህነት ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አጋልጦዋል።

አዳራሹ በፌዴራል ፖሊስ ተወጥሮ እየተደረገ ያለው ስብሰባ በእምነት አባቶች ላይ ውጥረት ለመፍጠር እና ሳይወዱ በግድ አስፈራርተው የሚፈልጉትን ውሳኔ ለማሳለፍ የተጠቀሙበት ዘዴ ነው ያሉት ምንጮቹ ፖሊሶች ግን የመጡበትን ምክንያት እንኳዋን እንደማያውቁም ገልፀዋል።

ዛሬ የቤተክህነት አመራር በሙሉ በአንድ ጎሳ የተያዘ በመሆኑ ስራ ለመስራት አልተቻለም እያሉ ሲተቹና ሲገልጹ የነበሩት አባቶች ከስብሰባው ሲወጡ በመልክ የማይታወቁ ሰዎች እያስፈራሩ እና እየዛቱባቸው አባ ጳውሎስ የሚያቀርቡትን ሀሳብ ብቻ እንዲደግፉ እያስጠነቀቁዋቸው መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ የአባ ጳውሎስ ቅርብ ነው የተባለ አንድ ግለሰብ የራሱን የደህንነት መዋቅር ዘርግቶ ጳጳሳቱን እያስፈራራ መሆኑን የቤተክህነት ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።

አሁንም በቤተክህነት ውስጥ ያለው የጎሳ አደረጃጀት በአዲስ መልክ ተጠርጎ አዲስ ድልድል ካልተሰራ በስተቀር ቤተክህነት ወደ ገደል እየገባች መሆኑን ጳጳሳቱ በምሬት እየተናገሩ ሲሆን ነባር የቤተክህነት ሰራተኞችም በሚደርስባቸው መድልኦ በሀዘን ተውጠው እንደሚገኙ ምንጮቹ ገልጸዋል።

በውጭ ሀገራት ተመድበው ሲሰሩ የነበሩት ጳጳሳት ቢመጡ የሚደርስባቸውን በደል እና እንግልት በማወቃቸው ባለንበት ሆነን የሲኖዶሱን ውሳኔ እንጠብቃለን በማለት ሳይመጡ መቅረታቸው የአባ ጳውሎስ አምባገነናዊ አስተዳደር እጅግ ወደ ባሰ አዘቅት እየወረደ መሆኑም ጭምር ያሳየ ነው ሲሉም ምንጮቹ ገልጸዋል።